# አምላክ በሰው ልጆች ላይ መከራ እንዲደርስ የፈቀደው ለምንድን ነው? (ክፍል 1)

ይህ ትምህርት የተመሠረተው ትክክለኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት ምንድን ነው? በተባለው መጽሐፍ ምዕራፍ 11 ላይ ሲሆን መጽሐፉ jw.org/am ላይ ይገኛል።

**ዓላማው፦ ምን ብለህ እንደምታምንና እንዲህ ያለ እምነት ልታዳብር የቻልክበትን ምክንያት ፈትሸህ ለማወቅ እንዲሁም መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምርና እምነትህን ለሌሎች ማስረዳት የምትችለው እንዴት እንደሆነ ለመመርመር።**



## ለሚደርስብን መከራ ተጠያቂው አምላክ ነው?

### 1 እምነትህን ፈትሽ

አንዳንድ ሰዎች ለዚህ ጥያቄ “አዎ” የሚል መልስ የሚሰጡት ለምን ይመስልሃል?

______________________________

አንዳንድ ሰዎች ለዚህ ጥያቄ “አይደለም” የሚል መልስ የሚሰጡት ለምን ይመስልሃል?

______________________________

አንተስ ምን ብለህ ታምናለህ?

______________________________

______________________________

እንዲህ ብለህ እንድታምን ያደረገህ ምንድን ነው?

______________________________

______________________________



www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 2 መጽሐፍ ቅዱስ ምን እንደሚያስተምር መርምር

**ይሖዋ መከራ እንዲደርስብን አይፈልግም።**
(የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 11 ከአንቀጽ 1-5 ተመልከት።)

### አንደኛ ጴጥሮስ 5:7ን አንብብ።

ይህ ጥቅስ ይሖዋ መከራ ሲደርስብን ማየት እንደማይፈልግ የሚጠቁመው እንዴት ነው?

______________________________

______________________________

______________________________

### ኢዮብ 34:10ን አንብብ።

በሰው ልጆች ላይ እየደረሰ ያለው መከራ መንስኤ አምላክ ነው?

______________________________

______________________________

______________________________



**አንድ አሽከርካሪ የትራፊክ ሕግ በመጣሱ፣ ተሽከርካሪውን የሠራው ፋብሪካ ተጠያቂ ሊሆን ይችላል?**
**ታዲያ የሰው ልጆች ላመጡት ችግር ፈጣሪ ተጠያቂ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው?**


www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## በሰው ልጆች ላይ እየደረሰ ያለው መከራ መንስኤ ሰይጣንና እሱ ያስነሳው ዓመፅ ነው።

(የመጽሐፍ ቅዱስ ትምህርት የተባለውን መጽሐፍ ምዕራፍ 11 ከአንቀጽ 6-9 ተመልከት።)

### አንደኛ ዮሐንስ 5:19ን እና ራእይ 12:9ን አንብብ።

እነዚህ ጥቅሶች መከራ እንዲደርስብን የሚፈልገው ሰይጣን መሆኑን የሚጠቁሙት እንዴት ነው?

### መክብብ 4:1ን፣ 8:9ን እና 9:11ን አንብብ።

ከሰይጣን ተጽዕኖ በተጨማሪ አንዳንድ ጊዜ መከራ የሚደርስብን ለምን ሊሆን ይችላል?

አምላክ መከራ እንዲደርስብን እንደማይፈልግ እንዲሁም መከራ ሲደርስብን እርዳታ እንደሚያደርግልን ማወቅህ የሚያጽናናህ ለምንድን ነው?


www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania

## 3 እምነትህን ለሌሎች አስረዳ

አንድ ሰው እንዲህ ቢልህ . . .

**አምላክ ጨካኝ ነው። ሰዎች እንዲሠቃዩ ይፈልጋል።**

እንዲህ ብለህ መመለስ ትችላለህ . . .

**በርካታ ሰዎች በዚህ ሐሳብ ይስማሙ ይሆናል። እኔ ግን ከዚህ የተለየ አመለካከት አለኝ፤ ምክንያቱም . . .**

________________________________________

________________________________________

ለግለሰቡ የትኛውን ጥቅስ ልታሳየው ትችላለህ?

________________________________________

የግለሰቡን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ጥቅስ ልታብራራ የምትችለው እንዴት ነው?

________________________________________

አንድ ሰው እንዲህ ቢልህ . . .

**ይህን ዓለም የሚቆጣጠረው አምላክ ነው፤ በመሆኑም በምድር ላይ የሚከናወኑት ነገሮች በሙሉ የእሱ ፈቃድ መሆን አለባቸው።**

እንዲህ ብለህ መመለስ ትችላለህ . . .

**በርካታ ሃይማኖቶች እንዲህ ብለው ያስተምራሉ። እኔ ግን ይህን ዓለም የሚቆጣጠረው አምላክ ሳይሆን ሰይጣን እንደሆነ አምናለሁ፤ ምክንያቱም . . .**

________________________________________

________________________________________

ለግለሰቡ የትኛውን ጥቅስ ልታሳየው ትችላለህ?

________________________________________

የግለሰቡን አመለካከት ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን ጥቅስ ልታብራራ የምትችለው እንዴት ነው?

________________________________________


www.jw.org/am © 2016 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania